# የእድገት ሙከራ ፕሮግራም ግምገማ

## ማጠቃለያ

ደራሲ፡- አቢ መ. ከድር፣ ማርታ ክብሩ፣ ኤምሊ ሻውብ እና ፋፋ ኢሳያስ



*Front cover image credit: Stewart Innes/Alamy Stock Photo*

# ዳራ




ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ኢትዮጵያውያን በተለይም ወጣት ሴቶች እና ልጃገረዶች የቤት ውስጥ ስራ ፍለጋ ወደ መካከለኛው ምስራቅ ይሰደዳሉ። እ.ኤ.አ በ2021 ወደ 839,224 የሚገመቱ ኢትዮጵያውያን ፍልሰተኞች በሌሎች አገሮች ይኖሩ እንደነበር ይገመታል። ከእነዚህ ፍልሰተኞች ውስጥ 46 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው። እንዲሁም በዝህው አመት (2021) ውስጥ 589,110 ፍልሰተኞች ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል። ከእነዚህ ከተመለሱት ፈልሰተኞች መካከል 62 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው[1]። ፍልሰተኛ ሴቶች በመዳረሻ አገራት ውስጥ ከፍተኛ ጥቃት፣ ብዝበዛ እና ግርድና ይደርስባቸዋል፡፡ እንዲሁም ወደ አገራቸው ኢትዮጵያ ሲመለሱ መልሰው-ለመቋቋም መቸገር፣ የደረሰባቸውን የመገለል ፈተናን ለመቋቋም መቸገር፣ የስራ እድል ውስንነት እና የጤና እክል ፈተናዎች ያጋጥማቸዋል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2015 ፍሪደም ፈንድ እና የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ አደጋ የሚያስከትለውን ፍልሰት ለመቀነስ እና ከተለያዩ ጥቃቶችና ብዝበዛዎች በህይወት የተረፋ ተመላሾችን ሁለንተናዊ ደስታን እና ጤናን ለማሻሻል በአዲስ አበባ እና በአማራ ክልል የድጋፍ አገልግሎት አቋቋመዋል። የዚህ ጥረት አካል የሆነው እ.ኤ.አ ከ2021 እስከ 2023 የተተገበረው 'እድገት' ፕሮግራም ለ240 ተመላሽ ሴቶች የቴክኒክ እና ሞያ ስልጠና በመስጠት፣ የስራ እድል እንዲያገኙ አስችሏቸዋል። እድገት ፕሮግራም ከሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር በመተባበር የመስተንግዶ አገልግሎት የስራ፣ የምግብ ዝግጅት እና የህጻናት እንክብካቤ ስልጠናዎችን ሰጥተዋል፡ ፡ በዚህ ፕሮግራም የታቀፋ ሰልጣኞች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማዕከል ያደረገ የስነ-ልቦና እና ሕፃናት ማቆያ አገልግሎት ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህ ተነሳሽነት ከህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በህይወት ለተረፋ ተመላሾች እና ከመደበኛው ሴክተር የስራ እድሎች ለተገለሉ ሌሎች ተጋላጭ ቡድኖች ዘላቂ የስራ እድሎችን መፍጠር ላይ ያተኩራል።

የእድገት ፕሮግራም ምዘና ጥናት፣ በፕሮግራሙ በተሳታፊ ሴቶች የስራ ስምሪት እና ዳግም ውህደት ላይ ያለውን ተጽእኖ በጥልቀት በመመልከት አዋጭነቱን እና ወጪ ቆጣቢነቱንም መርምሯል። ጥናቱ እድገት ፕሮገራምን ለማሳደግ እና ለማስፋፋት ይረዳ ዘንድ በፕሮግራሙ ትግበራ ወቅት የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን እና ምክረ ሀሳቦችን ለመለየት በጥልቀት ተመልክቷ፡፡ ግምገማው ከበርካታ ምንጮች የተገኘውን መረጃ/ዳታን አካትቷል፡-

- የፕሮግራሙ ሰነዶች እና የክትትል ሪፖርቶች፣
- 45 የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቆች እና ትኩረት ቡድን ውይይት የተካተቱ ከ21 የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች፣
- 61 የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችን ያሳተፈ ዳሰሳ ጥናት፣ እና
- ከአገር በቀል ባለድርሻ አካላት ጋር በተለይም የሴቶች የኢኮኖሚ ማጎልበቻ ባለሙያዎች፣ ድርጅት ሰራተኞች፣ አሰልጣኝ/ አገልግሎት ሰጪ/ ድርጅቶች፣ ፖሊሲ አውጪዎች እና ቀጣሪዎች ጋር የተደረገ ስምንት ቁልፍ የመረጃ ሰጭ ቃለመጠይቆች ተመልክቶአል።

1 የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት (2021)፡ እ.ኤ.አ. በ2021 የሰራተኛ ኃይል እና የፍልሰት ዳሰሳ ላይ የስታቲስቲክስ ሪፖርት https://www.ilo.org/surveyLib/index.php/catalog/7982/related-materials

# ቁልፍ ግኝቶች

## ስነ-ሕዝብ

በኢትዮጵያ ከተሞች ከሚኖሩት ከአብዛኛው የፍልሰተኛ ተመላሽ ሴቶች ጋር ሲነፃፀሩ፣ የእድገት ፕሮግራም ተሳታፊዎች የተወሰነ ያህል በዕድሜ የገፉ እና ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ናቸው[2]። አብዛኛዎቹ የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊዎች እድሜ ከ35 ዓመት[3] በታች ሲሆን፤ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን የአጠናቀቁ ናቸው። ከእነዚህ ሴቶች 59 በመቶው ያገቡ ሲሆኑ፤ አንድ አራተኛው ደግሞ ጨርሶ ትዳር ያልመሰረቱ ናቸው። አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ቢያንስ አንድ ልጅ ያላቸው ወላጆች ሲሆኑ፣ 59 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ በአራት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቤተሰብ አባላት ጋር ይኖራሉ፡፡ አማካይ የቤተሰብ ገቢ በወር ብር 6,565 (119 ዶላር) ሲሆን፣ የተሳታፊዎች የወር ገቢ ከብር 1,600 (29 ዶላር) እስከ ብር 19,000 (USD 344) ነው።

የእድገት ፕሮገራም ተሳታፊዎች በአማካኝ ለ6 ዓመታት በውጭ አገር በስራ ላይ የቆዩ ሲሆን፣ ይህ የቆይታ ግዜያቸው ከአንድ አመት እስከ 26 አመታት ድረስ ነው። አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ቢያንስ ሁለት ጊዜ ወደ ውጭ አገር የፈለሱ ናቸው። አንድ አምስተኛ የሚጠጉት ተሳታፊዎች ቢያንስ ለአስር አመት በውጭ አገር ሰርተዋል። 28 በመቶ የሚሆኑት ተሳታፊዎች በመካከለኛው ምስራቅ የፍልሰት ልምድ ያላቸው፣ በአሁኑ ጊዜ እዚያ የሚሰሩ ወይም ቀደም ሲል እዚያ ይሰሩ የነበሩ የቤተሰብ አባላት እንዳሏቸው ጠቁመዋል።

## የሥራ ተግዳሮቶች

ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱት ፍልሰተኞች በተለይም ሴቶች ስራን ለማግኘት ከፍተኛ ተግዳሮቶች ያጋጥማቸዋል፡፡ እነዚህ ተግዳሮቶች ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ፣ ማንበብና መጻፍ መቸገር እና መደበኛ ስልጠና እጦት፣ አማራጭ እድል እጦት እና በተመላሽ ፍልሰተኞች ላይ የሚደርስ መገለል እና መድሎ ናቸው። ፍልሰተኞች እራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን መርዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ብዙ ሀብት ሳይዙ መመለስ ብዙውን ጊዜ እንደ ውድቀት ይታያል። ከስደት የተመለሱት በተለይም ሴቶች በቀጣሪዎች ጥርጣሬ እና መድልዎ ይደርስባቸዋል፤ ይህም በተለይ በመደበኛ የስራ ዘርፍ የስራ እድላቸውን ያሳንሳል። ይህ መገለል ከባህላዊ የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎች እና የቤት ውስጥ ኃላፊነቶች ጋር ተዳምሮ የፍልሰት ተመላሽ ሴቶች የስራ እድሎችን የበለጠ በመገደብ ኢኮኖሚያዊ ተጋላጭነታቸውን ያባብሳል።





*Image credits, left to right: IMAGO/Xinhua; Angelov - stock.adobe.com*

2 የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት (2021)፡ እ.ኤ.አ. በ2021 የሰራተኛ ኃይል እና የፍልሰት ዳሰሳ ላይ የስታቲስቲክስ ሪፖርት https://www.ilo.org/surveyLib/index.php/catalog/7982/related-materials

3 አማካይ ዕድሜ: 32 ዓመት፤ የእድሜ ክልል፡ 29-35

## የፕሮግራም ልምድ

**ቁልፍ ግኞቶች**

- 96 በመቶ የሚሆኑ ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ተሳታፊዎች በኬዝ ማናጀሮች በተሰጣቸው ድጋፍ ረክተዋል።
- ሁሉም (100%) ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ተሳታፊዎች በእድገት ፕሮግራም ውስጥ ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር ህብረትን ፈጥረዋል፣ ጓደኝነትን መስርተዋል እንዲሁም እኩል የአካታችነት ስሜት ተሰምቷቸዋል።

ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ተሳታፊዎች በሁሉም የእድገት ፕሮግራም መርሃ-ግብሮች እና ተግባራት ከፍተኛ እርካታ እንዳላቸው ገልጸዋል። ተሳታፊዎች በአሰልጣኞች እና በኬዝ ማናጀሮች በሚደረጉት ድጋፍ ከፍተኛ እርካታ እንዳላቸው በመግለጽ በፕሮግራሙ ውስጥ የተካተቱ የድጋፍ ሥርዓቶች እና የአቻ ድጋፍ ጥምረቶች ያላቸውን አወንታዊ ተፅእኖ አፅንዖት ሰጥተዋል። ለዚህ የድጋፍ ስርዓት ዋጋ መስጠታቸውን አክለው በፕሮግራሙ ጠቃሚ ክህሎቶችን እና እውቀቶችን እንዳገኙ ተሳታፊዎች ሪፖርት አድርገዋል። እንደ የትራንስፖርት እና የመዋለ ሕፃናት ድጋፍ ያሉ ተጨማሪ አገልግሎቶች ለተሳታፊዎች በጣም ጠቃሚ መሆናቸው ተገልጸዋል። አብዛኞቹ ተሳታፊዎች በአጠቃላይ በፕሮግራሙ እርካታቸው ከፍተኛ መሆኑን ሲገልፁ፣ ጥቂቶቹ አንዳንድ ተግዳሮቶች ጠቁመዋል። እነዚህም የሕጻናት ማቆያ ውስንነት፣ የገንዘብ ድጋፍ ውስንነት እና በስልጠና ተቋማቱ ውስጥ ያሉ አቅርቦቶች እና መሳሪያዎች ውስን መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

> **በእድገት ሙከራ ፕሮግራም ውስጥ ያገኘሁት አንዱ ፋይዳ ከአቻ የፍልሰት ተመላሾች ጋር በድጋሚ መገናኘት እና ከእነርሱ ጋር ግዜን ማሳለፍ መቻል ነው።**
> ቃለ-መጠይቅ የተደረገላት ተሳታፊ

## የሥራ እድል ውጤቶች

**ቁልፍ ግኞቶች**


- ተሳታፊዎች በእድገት ፕሮግራም ውስጥ ከመሳተፋቸው በፊት ካከናወኗቸው ስራዎች ጋር ሲያነፃፅሩ ስለ የስራ ሁኔታቸው እና የወደፊት እድሎቻቸው የበለጠ አዎንታዊ ስሜት ተሰምቷቸዋል። ከቀደምት ስራዎቻቸው (46 በመቶ) ጋር ሲያነፃፅሩ፣ 98 በመቶ የሚሆኑት ተሳታፊዎች አዲሱን የስራ ሁኔታቸውን በደንብ እንደሚያውቁ ገልፀዋል።
- አማካይ የስራ ሰአት በሳምንት በአማካይ በ72 ሠዓታትንቀንሷል።
- የተሳታፊዎችን እሳቤ/ግምት ከስራ ገበያው እና ተጨባጭ ስራ እድሎች ጋር በተሻለ ሁኔታ ማመጣጠን ሊያስፈልግ ይችላል።

አብዛኛዎቹ የግምገማ ተሳታፊዎች የእድገት ፕሮግራም ለስራቸው የሚያስፈልጋቸውን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ እንዳስጨበጣቸው ተሰምቷቸዋል። በመማርያ ክፍል ውስጥ የተሰጣቸው ስልጠናም ሆነ የስራ ላይ ልምምድ ጠቃሚ መሆናቸውን አክለው ገልፀዋል። ነገር ግን፣ 92 በመቶ የሚሆኑት እንደ ከፍተኛ ደመወዝ፣ የሕጻናት እንክብካቤ ፍላጎቶች፣ የንግድ ሥራ ዕድገት እድሎች እና የሥራ ጫናን መቀነስ የመሳሰሉ ምክንያቶችን በመጥቀስ በግል ሥራ መሥራትን እንደሚመርጡ ሪፖርት አድርገዋል። 87 በመቶው የሚሆኑት ደግሞ በተለያየ የስራ ዘርፍ ቢሰሩ ይመርጡ እንደ ነበር ጠቅሰዋል። ነገር ግን እነዚህ አመለካከቶች ሁልጊዜ ከአካባቢው ኢኮኖሚ ጋር የተጣጣሙ ላይሆኑ ይችላሉ። እነኚህ ግኝቶች ድጋፍ እና የክህሎት ግንባታ ፕሮግራሙ ከተሳታፊዎች ፍላጎት ጋር መጣጣም እንዳለባቸው ያሳያሉ። ይህም ተሳታፊዎች በስራቸው የረኩ መሆናቸው ለማረጋገጥ ያለመ መሆን አለበት። እንዲሁም ተነሳሽነቶቹ ተሳታፊዎች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ውስጥ ስላለው የገቢ ደረጃዎች እና የሥራ ሁኔታዎችን አስመልክቶ ተጨባጭ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሊያደርጉ ይገባል።

> **በስልጠና ወቅት በክፍል ውስጥ ያገኘሁት እውቀት እና በስራ ላይ ልምምድ የተግባር እውቀት ጥምረት ለስራ በጥሩ ሁኔታ አዘጋጅቶኛል።**
> ቃለ-መጠይቅ የተደረገላት ተሳታፊ


ሴቶች በአዲሱ ሥራዎቻቸው በሳምንት በአማካይ 49 ሰዓታት እንደሚሰሩ ተናግረዋል ። ከዚህ ቀደም፣ በመካከለኛው ምስራቅ በሳምንት በአማካይ 128 ሰዓታት እና በኢትዮጵያ ደግሞ 63 ሰዓታት ይሰሩ ነበር። ተሳታፊዎች ከቀደምት ስራቸው ጋር ሲያነፃፅሩ

በስራ ሁኔታቸው ላይ ከፍተኛ መሻሻሎች መኖሩን አስተውለዋል። 98 በመቶ ራሳቸውን ችለው የመስራት ነፃነትን እና በስራ ቦታ ላይ ለሚደረጉ ውሳኔዎች አስተዋፅዖ ማድረግን ጨምሮ ስለ ስራቸው ውሳኔ ለማድረግ ስልጣን እንደተሰጣቸው ጠቅሰዋል። በተጨማሪም፣ ሁሉም (100%) ተሳታፊዎች በሥራ ቦታቸው እንደተከበሩ ተሰምቷቸዋል። እንዲሁም 84 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች እያከናወኑት ያለው የስራ ሁኔታ እና አፈፃፀማቸው ወደፊት አርኪ እድሎችን እንደሚያመጣላቸው ተስፋ እንዳላቸው ሪፖርት አድርገዋል (ሥዕላዊ መግለጫ 1)። ወጣት ተሳታፊዎች የስራ ሁኔታቸውን አስመልክቶ አዎንታዊ አመለካከት አላቸው (p=0.058)። በሌላ በኩል፣ በተለያየ ዘርፍ የመሥራት ፍላጎት እንዳላቸው የገለጹ ተሳታፊዎች የሥራ ሁኔታቸውን አስመልክቶ አሉታዊ አመለካከት አላቸው (p=0.070) እና በአሁኑ ስራዎቻቸው ለወደፊቱ መልካም እድሎችን እንደሚያመጣ በራስ መተማመን አልተሰማቸውም (p=0.086)።




***ሥዕላዊ መግለጫ 1: የተሳታፊዎች የሥራ ሁኔታ ዕይታ***

የተሳታፊዎች አማካይ ገቢ በወር ብር 3,995 (72 ዶላር) ሲሆን፣ ይህም ቀደም ሲል በሚሰሩት ስራ ይከፈላቸው ከነበረው ብር 5,512 (100 ዶላር) ያነሰ ነው። በተጨማሪም፣ 64 በመቶ የሚሆኑ ተሳታፊዎች ገቢያቸው ለፍጆታ “ከሚያስፈልገው በጣም ያነሰ” መሆኑን ሪፖርት አድርገዋል። የስራ እድል በሚገኙባቸው እንደ መስተንግዶ እና የምግብ ዝግጅት ያሉ ዘርፎች ከሶስት ወር የስራ ሙከራ ግዜ በኋላ የተሻለ ክፍያ ወይንም ደመወዝ ጭማሪ ማድረጉ የተለመደ ተግባር ነው። በቃለ-መጠይቁ ወቅት ሁሉም ምላሽ ሰጪዎች ይህንን የሙከራ ጊዜ ያጠናቀቁት አልነበሩም። ሥዕላዊ መግለጫ 2 በተቀጠሩ ተሳታፊዎች ሪፖርት የተደረገውን የገቢ ሁኔታ ያመላክታል። ሪፖርት የተደረገው ደሞዝ በኢትዮጵያ ከተሞች ሴቶች ከሚያገኙት አማካይ ገቢ (ብር 3,538፤ 64 ዶላር)[4] በመጠኑ ከፍ ያለ ነው፤ እናም ይህ በአዲስ አበባ[5] ያለውን የኑሮ ወጪዎችን ለመሸፈን በአለም አቀፉ የሰራተኛ ድርጅት (ILO) አስፈላጊ ነው ተብሎ ከተቀመጠው (ብር 3,282፣ 59 ዶላር) ከፍ ያለ መሆኑን ልብ ይበሉ።




***ሥዕላዊ መግለጫ 2: ተቀጥረው በስራ ላይ ያሉ የተሳታፊዎች ወርሃዊ ገቢ (ቁጥር= 44)***

4 የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት (2021)፡ እ.ኤ.አ. በ2021 የሰራተኛ ኃይል እና የፍልሰት ዳሰሳ ላይ የስታቲስቲክስ ሪፖርት፤ ከገጽ 221 እስከ 226። https://www.ilo.org/surveyLib/index.php/catalog/7982/related-materials


5 አለም አቀፉ የሰራተኛ ድርጅት (ILO) በኢትዮጵያ ውስጥ በአገር አቀፍ ደረጃ አምስት አባላት ያሉት ቤተሰብ መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላት በወር ብር 5,278 (95.63 ዶላር) እንደሚያስፈልግ ይገምታል። ይሁን እንጂ አዲስ አበባ ከተማ ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነጻጸር ቁልፍ ወጪዎች ከፍተኛ መሆኑንም ILO ይጠቁማል። ለምሳሌ በአዲስ አበባ አማካኝ ወርሃዊ የቤት ኪራይ ብር 2,080 (38 ዶላር) ሲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ ብር 794 ብር (14 ዶላር) ነው። ምንጭ፡ ILO (2021)፡ በኢትዮጵያ የሰራተኞች እና የቤተሰቦቻቸው ፍላጎት ግምት (ገጽ 41-27)። በዚህ ሊንክ ያገኙታል፡ https://www.ilo.org/wcmsp5/groups/public/---ed_protect/---protrav/---travail/documents/projectdocumentation/wcms_826322.pdf

# የመልሶ ማቋቋም ውጤቶች

**ቁልፍ ግኞቶች**

- 97 በመቶው የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊዎች በስልጠና ያካበቱትን እውቀቶችን በመጠቀም ካለፋት ከፍተኛ የስነ-ልቦና ጉዳቶች ለማገገም ችለዋል፤ እንዲሁም 93 በመቶ ደግሞ በስልጠና ያካበቱትን እውቀት በመጠቀም እፍረትን፣ ውድቀትን እና ጭንቀትን መቀነስ ችለዋል።
- 94 በመቶ የሚሆኑት የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊዎች ወደ ኢትዮጵያ በተመለሱበት ወቅት ለራሳቸው ይሰጡት ከነበረው ዝቅተኛ አመለካከት ማሻሻልን አሳይተዋል::
- 59 በመቶው የዳሰሳ ጥናት ተሳታፊዎች ዳግም ፍልሰትን ይመርጣሉ ፣ ነገር ግን እንደገና ወደ መካከለኛው ምስራቅ ዳግም መፈለስ እንደምፈልጉ የጠቆሙት 18 በመቶ ብቻ ናቸው።

ሁሉም ማለት በሚቻል ደረጃ የዳሰሳ ጥናቱ ተሳታፊዎች ከእድገት ፕሮግራም ያገኙትን እውቀት በመጠቀም ካለፋት ከፍተኛ የስነ-ልቦና ጉዳቶች አገግመዋል፣ ለራሳቸው ይሰጡት ከነበረው አሉታዊ አመለካከቶች ማሻሻልን አሳይተዋል እና ወደ ኢትዮጵያ በተመለሱት ወቅት ለራሳቸው ይሰጡት ከነበረው ዝቅተኛ አመለካከት በመውጣት አሁን አስፈላጊ ሰው እንደሆኑ ተሰምቷቸዋል:: በተመሳሳይ መልኩ በርካታ ተሳታፊዎች ውሳኔ መስጠትን፣ ነፃነታቸውን ማረጋገጥን፣ እና ግባቸውን ማሳካት እንደሚችሉ ሪፖርት አድርገዋል (ሥዕላዊ መግለጫ 3ን ይመልከቱ)።




***ሥዕላዊ መግለጫ 3: የተሳታፊዎች መልሶ ማቋቋም ውጤቶች***

> **በእድገት ፕሮግራም አማካኝነት ጠንካራ በራስ የመተማመን ስሜትን ማዳበር እና የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታዬን ማሻሻል ችያለሁ፤ ይህም በግል እና በሙያዬ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ አድርጓል.**
> ቃለ-መጠይቅ የተደረገላት ተሳታፊ

ምንም እንኳን አወንታዊ ውጤቶች ቢገኙም፣ 59 በመቶ የሚሆኑ የዳሰሳ ጥናቱ ተሳታፊዎች ዳግም መፈለስ እንደሚፈልጉ ጥናቱ ያሳያል፤ 18 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ዳግም ቢፈልሱ መካከለኛው ምስራቅን መድረሻ እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል። ዳግም የመፈለስ እድልን አስመልክቶ በተሳታፊዎች መካከል በእድሜ፣ በትውልድ ቦታ ወይም በቀድሞ መዳረሻ አገራት ልዩነት የላቸውም። ነገር ግን፣ ልጆች ያሏቸው ሴቶች ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገር ($p=0.086$) ወይም ወደ የትኛውም የአለም ክፍል ($p=0.092$) ዳግም ለመፍለስ የመፈለግ እሳቤያቸው ልጅ ከሌላቸው ሴቶች በመጠኑ ከፍ ያለ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል። ኢትዮጵያ ውስጥ ተመላሾችን በተሳካ ሁኔታ መልሰው ለማቋቋም እና ያልተፈለገ ወይም ያልተማከረ ዳግም ፍልሰት ውስጥ እንዳይገቡ ለመከላከል ድጋፍ ሰጪ ማህበራዊ ኔትዎርኮች እና ምቹ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ያላቸው ሚና ወሳኝ መሆኑን ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች በአጽዕኖት መክረዋል።

# መደምደምያ እና ምክረ-ሀሳቦች

እድገት የሙከራ ኘሮግራም ለፍልሰት ተመላሽ ሴቶች የሙያ ስልጠና በብቃት በመስጠት መደበኛ ስራ እንዲሸጋገሩ አመቻችቶላቸዋል። ተሳታፊዎቹ በስራ ሁኔታቸው መደሰታቸውን ገልጸው ለራሳቸው የሚሰጡት ቦታ ከፍ ብሷል፣ በራስ መተማነቻቸው ጨምሯል እና ካለፋባቸው ከፍተኛ የስነ-ልቦና ጉዳት ማገገም ችሏል፤ ይህም ለተሳታፊዎች የተደረገውን ሁለንተናዊ የስነ-ልቦና ድጋፍ እና በማህበረሰብ መልሶ ማቋቋም ላይ የተሰራውን የፕሮግራሙን አዎንታዊ ተጽዕኖ ያመለክታል። የዚህ ግምገማ ግኝቶች እና አስተያየቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገውን የሴት ተመላሾች መልሶ ማቋቋም የሽግግር ሂደትን ለመደገፍ እና ከፍልሰት ተመላሽ ሴቶችን ለማብቃት የሚደረጉ ጥረቶች ምክረ ሀሳቦችን እና መልካም ተሞክሮዎችን ይሰጣሉ።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ምክረ-ሀሳቦችን የሚያረጋግጡ ተጨማሪ ማስረጃዎች በሚቀጥለው ሙሉ ሪፖርት ውስጥ ይካተታሉ።

1 **ከተሳታፊዎችና ከቀጣሪዎች ጋር ቀጣይነት ያለው ግንኙነት በማድረግ እና ከነባራዊ የስራ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም እድገት ፕሮግራምን ማስቀጠል።** ሁሉም ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች እና አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች እንደገልጹት የእድገት ፕሮግራም ተደግሞ እና ሰፋ ባለ መልኩ ብዙ ኢትዮጵያውያን የፍልሰት ተመላሾችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ጠቁመዋል። ፕሮግራሙ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ተመላሽ ሴቶች ተደረሸ ቢሆን አዎንታዊ ተጽእኖ ለማሳደር ስላለው አቅም ሰፊ እውቅና ሰጥተውታል።

2 **ሰራተኞቹ በአዲሶቹ ስራዎቻቸው ላይ እንዲቆዩ ለማስቻል፣ ቀጣሪዎች የተሻለ የስራ አካባቢና ሁኔታ እንዲፈጥሩ ማበረታታት።** ተሳታፊዎች እና ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች በእድገት በኩል የሚገኙ የስራ እድሎች በተለይም በአገልግሎትሰጪ ኢንዱስትሪ ውስጥ ሁልጊዜ ተመራጭ የማይሆኑበት ምክንያት አብራርተዋል። የእነዚህን የሥራ ዓይነቶች ክብርና እውቅና ከፍ ለማድረግ አንዳንድ ግዴታዎች ወደ ቀጣሪዎች በተለይም ባለአራት እና ባለ አምስት ኮከብ ሆቴሎች ሊሸጋገር ይገባል፤ ምክንቱም እነዚህ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ሆቴሎች በመደበኛ ሴክተር ውስጥ የሴቶችን የሥራ ስምሪት ለማሳደግ ፍላጎት አሳይተዋል። ይህ ቁርጠኝነት ቀደም ሲል በእድገት ምሩቃን በተያዙ የስራ መደቦች ላይ ለአዲስ ተቀጣሪዎች ዝቅተኛ ደሞዝ ላይ በጋራ በመነጋገር መወሰን (ምንም እንኳን ዝቅተኛ ደመወዝ መነሻ በህግ ባይጠየቅም)፣ ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞችን መስጠት እና ለፕሮግራሙ ምሩቃን በየዓመቱ የተወሰኑ አዳዲስ የስራ ክፍት ቦታዎችን መስጠት/እድገት መስጠትን ሊያካትቱ ይችላሉ። እድገት ፕሮግራም ምሩቃኑን በተቀጠሩበት የስራ መደብ ላይ እንዲቆዩ ለማስቻል ወይም በሙያቸው ኩራት እንዲሰማቸው ለማሳደግ ከአሰሪዎች ጋር መተባበር አለበት። ይህም እንደ ስልጠና ሳጠናቀቁ ሰልጣኞች የምርቃት ምርሀ-ግብር በማዘጋጀት እውቅና መስጠት፣ ስኬቶቻቸውን በህዝብ ፊት እውቅና መስጠት፣ ለከፍተኛ ደሞዝ ሥራ እድገት መንገዶችን ማሳየት እና በቲፕ እና በአገልግሎት ክፍያዎች ዙሪያ ግንዛቤዎቻቸውን በማሳደግ የአገልግሎት የኢንዱስትሪ ደረጃዎችን ወደ ተሻለ ሰራተኛ ተኮር ማሳደግ ይረዳል።

3 **በእድገት ፕሮግራም ውስጥ ለሚሳተፉ ተመላሾች የቤተሰቦቻቸውን ድጋፍ ለመጨመር ይረዳ ዘንድ የቤት ውስጥ ሁኔታዎቻቸውን ለመረዳት ጥልቅ ቃለ-መጠይቆችን ያድርጉ።** በእድገት ውስጥ ከተጠበቀው በላይ ሆኖ የተገኘው አንዱ ቁልፍ ግኝት የተሳታፊዎች ምልመላ እና ምዝገባ በከፍተኛ ሁኔታ በኬዝ ሰራተኞች ድጋፍ ላይ የተደገፈ መሆኑ ነው - እሱም ኬዝ ማናጀሮች ከተሳታፊዎች ባሎች ወይም ቤተሰብ ውስጥ ካሉ ሌሎች ውሳኔ ሰጪዎች ጋር ሰፋ ያለና በቅርበት ግኑኝነት ማድረጋቸው ነው። ቋሚ ስራ ያላቸው ተሳታፊዎች ደመወዝ ከሚጠበቁት ያነሰ በመሆኑ ባሎች ወይም ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሌሎች ውሳኔ ሰጪዎች ተነሳሽነት ይቀንሳል። በረጅም ጊዜ ውስጥ የደመወዝ እድገት የሚጠበቅ ቢሆንም እንኳን፣ ይህ የእድገት ምሩቃን በስራ ላይ ቆይታን ማረጋገጥ በቤተሰብ ውሳኔ ሰጪዎች ላይ ያለውን ጉጉትና ተስፋን ያመነምናል። ስለዚህ፣ የቤተሰብ ውሳኔ ሰጪ ጉጉትና ተስፋ በአሉታዊም ሆነ በአዎንታዊ የሚጎዱትን መመርመር፣ የረጅም ጊዜ ፕሮግራም ዘለቄታን በሚያስደንቅ ሁኔታ ያጠናክራል።

4 **የስድስት ወራት በስራ ላይ ቆይታ በኋላ ድጎማዎችን ወይም የገንዘብ ድጋፎችን ለማድረግ ተጋላጭነቶችን እና/ወይም የገቢ ክፍተቶችን የሚለዩበት መስፈርቶችን ማዘጋጀት።** በሥራ ላይ የግዜ ቆይታዎቻቸው ምንም ይሁን ምን ሁሉንም ድጋፎች ለሁሉም ተሳታፊዎች በእኩልነት ከማቅረብ ይልቅ፣ ለስድስት ወራት በስራ ላይ ቆይታዎቻቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ ወጪ ቆጣቢ ስትራቴጂን በመጠቀም የእያንዳንዳንቻው ጉዳይ መመልከት እና የትኞቹ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጋቸው ለመወሰን መመዘኛዎችን ማዘጋጀትና መጠቀም። በግምገማው የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ረጅም እና ቀጣይነት ያለው ድጋፍ አስፈላጊነት በሁለቱም ተሳታፊዎች እና ባለድርሻ አካላት ተጠቅሰዋል።

**5** **ለስራ ላይ ልምምድ ረዘም ያለ ግዜ መስጠት።** አንዳንድ ተሳታፊዎች ስልጠናው በተለይም የፕሮግራሙ አካል የሆነው በስራ ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ የተሰጣቸው ግዜ ተቀጥረው እየሰሩ ላሉት ስራ በበቂ ሁኔታ እንዳላዘጋጃቸውና በቂ ክህሎት እንዳላስጨበጣቸው ሪፖርት አድርገዋል። በተመሳሳይ መልኩ፣ ይህ ረዘም ያለ በስራ ላይ ልምምድ ግዜ በቀጣሪዎች ዘንድ በበጎነት ሊወሰድ ይችላል።

**6** **በቅድመ-ምዝገባ ወቅት ከቴክኒክና ሙያ ስልጠና ድርጅቶች ምን እንደሚጠበቅ ተጨማሪ መረጃዎችን ለእጩ ሰልጣኞች መስጠት።** የተወሰኑ ተሳታፊዎች የሙያ ስልጠናቸውን አስመልክቶ ከቴክንክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የተጋነነ አገልግሎቶችን ይጠብቁ ነበር፤ ለምሳሌ ፕሮግራሙ ከሚያቀርበው የስልጠና አይነቶች በጣም ከፍያለ ስልጠና እንዲሰጣቸው ይጠይቁ ነበር:: በመረጡት የሙያ ስልጠና በተለይም በመስተንግዶ እንዳልተደሰቱ የገለጹ ተሳታፊዎች በፕሮግራሙ መጀመሪያ ላይ ስላሉት የሙያ ስልጠና አማራጭ አይነቶች እና የውጭ ሪፈራሎች (ለምሳሌ ስራ ፈጠራና እንግሊዘኛ ቋንቋን ወደሚሰጡት መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት እንዲሄዱ ጥቆማ መስጠት) ላይ የበለጠ መረጃ ቢሰጣቸው ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችሉ ነበር። ይህም በእድገት ፕሮግራም ምልመላ ወቅት እንደ ምርጥ ወይም ብቸኛ አማራጭ አድርጎ በማቅረብ የሚመጣውን ጫና ይቀንስ ነበር። ተሳታፊዎቹ በመረጡት የሥራ መስክ ውስጥ ስላለው የሥራ መዋቅርና ደመወዝ ላይ ተጨማሪ መረጃን መስጠት ይጠቅማቸው ነበር።

**7** **በሌሎች የሥራ ዘርፎች ስላሉት የስራ እድሎችን ማሰስ::** የትኞቹ የስራ ዘርፎች ለእድገት ወይም ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ተደራሽ ሊሆኑ እንደሚችሉ ዳሰሳ ማድረግ ጠቃሚ ነው። በሆቴል እንዱስትሪ ዘርፍ ስልጠና የወሰዱ በርካታ ተሳታፊዎች በሌሎች የስራ አይነቶች የስ ፍላጎት እንዳላቸው ጠቅሰዋል፤ ይህም ደግሞ በጊዜ ሂደት ሥራቸውን ሊለቁ እንደሚችሉ ማሳያ ልሆን ይችላል። እድገት ፕሮግራም ሰፋ ባለ መልኩ ለተለያዩ ዘርፎች ተስማሚ ሊሆን የሚችል የስልጠና አይነቶች ቢያካትት መልካም መሆኑን በተናጥል ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው በርካታ ተሳታፊዎች ጠቁመዋል። ዕምቅ የእድገት ተሳታፊዎችን ቁጥር ከግምት ውስጥ በማስገባት፡ በተመረጡት ኢንዱስትሪዎች የእጩ ስራ ፈላጊዎች ቁጥር ከመጠን በላይ እንዳይሆን ለመከላከል መካከለኛ እና ረዥም ጊዜ እቅድ በማውጣት ይተግብሩ። ከዘላቂነት አንፃር በሌሎች ተፈላጊ ዘርፎች ስልጠናዎችን ማካተት እና በእነዚያ ዘርፎች ውስጥ ለስራ ስምሪት የተሳታፊዎችን ተወዳዳሪነት ማሳደግ አስፈላጊ ነው።

**8** **ኢንተርፕረነርሺፕ ተኮር ሞጁሎችን እና ድጋፎችን ያካትቱ።** አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ለግል ስራ እና ስራ-ፈጠራ ፍላጎት እንዳላቸው አሳይተዋል፣ ይህም በገንዘብ ረገድ ትርፋማነትን፣ ብዙም የማያደክም፣ እና የስራ ሰዓት ነፃነት ይኖረዋል ብለው በማሰብ ነው:: ቁልፍ ባለድርሻ አካላት አንዳንድ ተያይዘው የሚመጡ አደጋዎች መኖራቸውን ቢያምኑበትም፣ ስራ ፈጠራ ለተመላሽ ሴቶች የተሳካ የስራ ሽግግር መሆን እንደሚችል ተወያይተዋል። የስልጠና ተቋማቱ የኢንተርፕረነርሺፕ ሞጁሎችን በእድገት የስልጠና መርሀ-ግብር ውስጥ ለማካተት ሊያስቡበት ይችላሉ። ይሁን እንጂ ተሳታፊዎች በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ በሥራ ገበያ ውስጥ ከሥራ ፈጠራ ጋር የተያያዙትን መሰናክሎች እና አደጋዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ማስጨበጥ ተገቢ ነው። የደመወዝ ሥራ ጋር ሲነፃፀር የሚያስከትለውን አደጋ እና ትክክለኛ የትርፋማነት እድል በተለይም በግል ሥራ ላይ በማተኮር ከሥራ ፈጣራ ጋር የተያያዙ የተዛባ አመለካከቶችን ለማጥራት ተጨማሪ ስልጠና ሊሰጥ ይችላል። የስራ ፈጠራ ስልጠና ለሚፈልጉ እጩ ተመዝጋቢዎች፣ ይህንኑ ስልጠና ወደሚሰጡ ተቋማት እንዲሄዱ ጥቆማ መስጠት በስራ ፈጠራ እና በቅጥር ስራ መካከል ያለውን ልዩነት ለማስተካከል ይረዳል።

**9** **የተመላሾች አቻ-ለ-አቻ ኔትዎርክ እና የማህበረሰብ ትስስር ማመቻቸት።** እንደ እድገት ባሉ ፕሮግራሞች ውስጥ የተሳተፉ የተመላሾች ኔትዎርክ የብርታት ምንጭ በመሆን፣ ከማህበረሰቡ ድጋፍ ለሚሹ ከህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በህይወት የተረፉ ሰዎች ዘላቂ ተሳትፎን ሊያረጋግጥ ይችላል። ከሌሎች ተመላሽ ሴቶች ጋር የመገናኘት እድል እንዴት እንደጠቀማቸው ተሳታፊዎቹ ጠቅሰዋል። እንደነዚህ ያሉት የድጋፍ ሥርዓቶች የተመላሽ ሴቶችን ጥቅም በተለይም ሥነ ልቦናዊ እና ሁለንተናዊ የኢኮኖሚዊ ተጠቃሚነታቸውን በዘለቄታ ሊያረጋግጡ የሚችሉ ናቸው። ወደፊት የሚደረጉ ተሳትፎዎች እነዚህን ግንኙነቶች በማበረታታት እና በማሳደግ እንዲሁም ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር መቀጠል አለበት።

**10** **ከኢትዮጵያ ውጭ ወደ አውሮፓ እና ሌሎች ተመራጭ መዳረሻ ክልሎች ለሚደረጉ ዳግም ፍልሰት አስመልክቶ የተሸለ ግንዛቤ እና ክህሎቶችን መስጠት።** በተለይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተሳታፊዎች በተለይም ወደ ከዚህ ቀደም ያልሄዱበት የአለም አገራት ዳግም መፈለስ እንደሚችሉ ወይም በጣም እንደሚፈልጉ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም፣ አብዛኞቹ ተሳታፊዎች በሌሎች የስራ ዘርፍ መሰማራትን እንደሚመርጡ ከተገለጸው እውነታ ጋር ተዳምሮ ተሳታፊዎች በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገራት ያሉትን የስራ እድሎችን እንዲያውቁ ማገዝ እድገት ፕሮግራም ከሚተገብሩ ድርጅቶች የሚጠበቅ ይሆናል። ይህ በተለይ ለሌሎች ክልሎች የስራ ገበያዎች አግባብነት ያለው ሲሆን ተሳታፊዎቹ በአዲስ መዳረሻ ሀገር ውስጥ ስላለው ስኬታማ ቆይታ ወይም የሥራ ስምሪት ያላቸው እውቀት እምብዛም ሊሆን ይችላል:: ተሳታፊዎች የማይገኙላቸውን እድሎች እንዲገነዘቡ መርዳት ብስጭትን ለመቆጣጠር እና ደህንነቱ ያልተጠበቀ ወይም መደበኛ ያልሆነ ዳግም ፍልሰትን ለመከላከል ወሳኝ ሊሆን ይችላል።

11 **ውሳኔ ሰጪ አካላት ለተመላሾች ድጋፍ ቅድሚያ እንዲሰጡ መሟገት።** በአሁኑ ጊዜ የተመላሾች ሁኔታ ለኢትዮጵያውያን ውሳኔ ሰጪዎች ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ አለመሆኑን በርካታ ቁልፍ መረጃ ሰጭዎች ተናግረዋል። እንዲሁም ከፍልሰት የተመለሱ ሴቶች የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች በተመለከተ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆኑን ብዙ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች አክለው ገልፀዋል። ለተመላሽ ሴቶች የሚሰጠውን ድጋፍ ግንዛቤ ለመስጠት በማስረጃ የተደገፈ ተሟጋችነትን እንደ ጠቃሚ መሳሪያ ይጠቀሙ፤ እንዲሁም ለተመላሽ ሴቶች ድጋፍ ለሚያደግርጉ እንደ እድገት ፕሮግራም ያሉ ፕሮግራሞችን ይደግፉ።

12 **ሥርዓተ-ፆታን ማዕከልና ለውጥ አካሔድን ይከተሉ።** በኢትዮጵያ ፍልሰት ተመላሽ ሴቶች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩትን የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን በተለይም በሥራ እና በመሰል ፕሮግራሞች ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ መገምገም እድገት ፕሮግራምን ይጠቅመው ነበር። ልማድ፣ ሴቶች በቤት ውስጥ እና ከቤት ውጭ የሚጫወቱትን ሚና፣ የተፈቀደላቸውን የስራ አይነቶች፣ እና ያለክፍያ የሚሰሩ ስራዎች እንደ እንክብካቤና የቤት ውስጥ ሥራን ቀዳሚ የሴቶች ኃላፊነት አድርጎ ይደነግጋል። ይህም ሴቶች ወደ በመደበኛ ሥራ በተቀመጠው የሥራ ሰዓቶች እና ቦታዎች የመሰማራት እድሎቻቸውን ሊገድብ ይችላል፤ በመሆኑም የግል ስራን እንደ አማራጭ እንዲወስዱ ሊያደርጋቸው ይችላል። በተጨማሪም ትራንስፖርት አገልግሎት በማይሰጥባቸው ስራዎች ወይም ተዓማኒ የትራንስፖርት አገልግሎት በሌለበት በተለይም በምሽት ወደ ሥራ መሄድ እና መመለስ ለሴቶች አደገኛ ሊሆን ይችላል።

13 **የፕሮግራም ተፅእኖዎችን እና ክፍተቶችን ለመለካት ተጨማሪ ምርምር ያካሂዱ።** ምንም እንኳን የእድገት ሙከራ ፕሮግራም ውጤቶች ተስፋ ሰጪ ቢሆኑም፣ ትርጉም ያለውን የፕሮግራሙን[6] ተፅዕኖ ለመረዳት፣ የረጅም ጊዜ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ተሳታፊዎችን[7] ያሳተፈ ግምገማ ያስፈልጋል። ይህ ግምገማ በፕሮግራሙ ውስጥ የቆዩ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎችንና በፕሮግራሙ በመሀል ያቋረጡ ተሳታፊዎችን ሊያካትት ይችላል። እንዲሁም ግምገማው በግዜ ሂደት ውስጥ ስላለው የተሳታፊዎች የስራ ሁኔታ፣ ገቢያቸውን እና ሁለንተናዊ ደስታቸውን ለመገምገምና ለማነፃፀር የፕሮግራሙ ተሳታፊ ያልሆኑ ሰዎችን ሊያካትት ይችላል። በሐሳብ ደረጃ፣ ግምገማው ቢያንስ ከ500 ግለሰቦች[8] መረጃን ማካተት አለበት። በዚህ ግምገማ ወቅት፣ አብዛኛው ተሳታፊዎች በስራ ላይ የግዜ ቆይታቸው ከስድስት ወር በታች ስለሆነ፣ እድገት ፕሮግራም ተሳታፊዎች ላይ ስላመጣው ዘላቂ ተፅዕኖ ላይ አስተያየት ለመስጠት አዳጋች ሆኖብናል፡፡ የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች በስራ ሁኔታቸው፣ ገቢያቸው እና ሁለንተናዊ መልሶ ማቋቋም ላይ ያላቸውን እርካታ በትክክል ለመለካት ወደፊት የሚደረጉ ጥናቶች የንፅፅር መረጃዎችን ማካተት ይጠበቅባቸዋል።

6 Alfonsi et al. (2020) Tackling Youth Unemployment: Evidence from a labour market experiment in Uganda, Econometrica, Vol.88,No.6(November),2369–2414. I

7 Kluve, J., Puerto, S., Robalino, D., Romero, J. M., Rother, F., Stöterau, J., Weidenkaff, F. and Witte, M. (2019). Do youth employment programs improve labor market outcomes? A quantitative review. World Development, 114, 237–53.

8 Hirshleifer, S., McKenzie, D., Almeida, R. and Ridao-Cano, C. (2016). The impact of vocational training for the unemployed: experimental evidence from Turkey. Economic Journal, 127, 2115–46.

# ራዕይ

ራዕያችን ከባርነት የፀዳች
አለምን ማየት ነው።

# ተልዕኮ

የእኛ ተልዕኮ ባርነትን ለማስወገድ
የሚያስፈልገውን እውቀት፣ ሀብት እና
ፋላጎት ማሰባሰብ ነው።


**The Freedom Fund (UK)**
Lower Ground
Caledonia House
223 Pentonville Rd
London, N1 9NG
+44 20 3777 2200

**The Freedom Fund (US)**
315 Flatbush Avenue
#406
Brooklyn, NY 11217
USA
+1 929 224 2448

www.freedomfund.org
info@freedomfund.org
@Freedom_Fund



The Freedom Fund is a United States 501(c)(3) public charity (EIN number 30-0805768).
The Freedom Fund UK is a company limited by guarantee registered in England and Wales (company number 08926428) and a registered UK charity (registration number 1158838).